## የፒስካኝ ድርጅታዊ መዋቅር፣

በአገር አቀፍ ደረጃ የአ/ግ/ሚ/ር የፒስካኝ አስተባባሪና መሪ ተቋም ነው፡፡ ዋና ሥራውም፣

እንደፒስካኝ ያሉ የአ/ግ/ኘሮግራሞችን ይመራል

የአፈፃፀም ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና መመሪያ ያወጣል

ኘሮግራሞች ከሴክተር ዕቅዶችና ስትራቴጂዎች ጋር መቀናጀታቸውን ያረጋግጣል፡፡

ለክልሎች የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል

የኘሮግራሞቹን አፈፃፀም ይከታተላል፣ በስሩም የፌዴራል የቴክኒክ ኮሚቴ አቋቁሞ የኘሮግራሙን የቀን ከቀን አፈፃፀም ይከታተላል ይመራል፡፡

### 4.1 የፌዴራል ፒስካኝ የቴክኒክ ኮሚቴ፣

የቴክኒክ ኮሚቴው በፌዴራል አ/ግንባታ ሚ/ር ኘሮግራምን የሚመራ ሆኖ 6ቱንም ኘሮግራሞች የሚመሩ ዳይሬክተሮች አባል ናቸው በተጨማሪም፡-

የፋ/ኢ/ል/ሚ/ር ተወካይ አባል

በፌዴራል ፋ/ኢ/ል/ሚ/ር የበጀት መምሪያ ኃላፊ አባል

በፌዴራል ፋ/ኢ/ል/ሚ/ር የብድር ገንዘብ ዩኒት አባል

የፌዴራል ጉዳዮች ሚ/ር ተወካይ አባል

የጠቅላይ ፍርድ ቤት ተወካይ አባል

የገቢዎች ሚኒስቴር ተወካይ አባል

የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ባለስልጣን ተወካይ የቴ/ኮሚቴው አባል በመሆን የሚያገለግሉ ሲሆን በPIP ውስጥ የየራሳቸው የስራ ድርሻና የቴ/ኮሚቴው የሥራ ድርሻ ተዘርዝሯል፡፡

### 4.2 ክልላዊ የፒስካኝ ድርጅታዊ መዋቅር

በሁሉም ክልሎች የአቅም ግንባታ ቢሮ ኘሮግራሙን በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፡፡

የቴክኒክ ኮሚቴውን ያስተባብራል ይመራል፡፡

በቢሮው ውስጥ የኘላንና ኘሮግራም ወይም አቻ መምሪያ ያቋቁማል በውስጡም የግዢ ዴስክ /ኮሚቴ/ ያቋቁማል 2 የግዥ ባለሙያዎች ይቀጠራሉ ያማክራሉ ይሠራሉ፡፡

በቴክኒክ ኮሚቴ ተሰርተው የሚቀርቡ የኘሮግራም ዕቅዶችን ይገመግማል ለካቢኔ ያቀርባል ያስወስናል፡፡

በየኘሮግራሞቹ ለሚከናወኑ ተግባራት ክፍያ እንዲፈፀም ለፋይናንስ ቢሮ ጥያቄ ያቀርባል፡-

**የክልሎች የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት፡-**

የኘላንና ኘሮግራም /አቻ/ መምሪያ አባልና የቴክኒክ ኮሚቴው ፀሐፊ /በክልላችን የአቅም ግንባታ ኘሮግራሞች መምሪያ ነው/

የፋ/ኢ/ል/ማስ/ቢሮ ተወካይ አባል

የን/ኢ/ክ/ል/ማስ/ቢሮ ተወካይ አባል

የፍትህ ቢሮ ተወካይ አባል

የ6ቱ ንዑሳን ኘሮግራሞች ኃላፊዎች /Focal persons/ አባል ናቸው፡፡ የእያንዳንዱ የስራ ድርሻ በ" PIP " ተዘርዝሯል፡፡

### 4.3 የክልሎች ኘላንና ኘሮግራም ዳይሬክቶሬት/ አቻ መምሪያ / ከ PIP ገጽ 17

መምሪያው በክልሉ የቴክኒክ ኮሚቴው ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ከፌዴራል አቻ መምሪያ /ዳይሬክቶሬት/ ጋር የስራ ግንኙነት ያደርጋል፡፡ በየክልሉ የሚገኘው ይህ መምሪያ የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉት፡-

የፒስካኝ መመሪያዎችና የክልሉን ተዛማጅ መመሪያዎች ያስፈፅማል፣

ለቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ኘሮግራሞች የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ጥራትና የስራ ቅንጅት አፈፃፀምን ይከታተላል፡፡

ዕቅዶች በተሳትፎ መሠራታቸውን ያረጋግጣል፣፣ ተሳትፎአዊ አሠራር እንዲጐለብት ያደርጋል፡፡

በቴክኒክ ኮሚቴዎች ውስጥ የአሠራር ቅንጅት ይፈጥራል፡፡

ስልጠና፣ ጨረታና ግዥዎች በ6ቱ ኘሮግራሞች ቅንጅትና ልዩ ባህሪይ ያላቸው ደግሞ በተናጠል በተገቢው

እንዲከናወኑ ያደራጃል፣ የአመራር ድጋፍ ይሰጣል፡፡

ተከታታይና ዝርዝር የኘሮግራሞች ክትትል በቴክኒክ ኮሚቴው እንዲደረግ ድጋፍ ይሰጣል ያመቻቻል፡፡

በፕሮግራሙ አፈጻጸም መልካም ግንኙነትና የለውጥ አመራር ስትራቴጂን ተግባራዊ ያደርጋል ፡፡

የሩብ ፤ የግማሽ ዓመትና የዓመት የፕሮግራሞች አፈጻጸም ሪፖርት ያዘጋጃል ያቀናጃል በቢሮው በኩል ለሚመለከታቸው ያስተላልፋ

የክልሉን የክትትልና ግምገማ ወዘተ ሥራዎች ያመቻቻል ፤ ያስፈጽማል

## 4.4 <u>የግዥ ዴስክ /ኮሚቴ/ በ " PIP " ገጽ 17 ይገኛል /</u>

የግዥ ዴስክ በቢሮው የሚቋቋም የግዥ ኮሚቴ ሲሆን ሁለት የግዥ አማካሪዎች / Local procurement specialist / አብረውት እንዲሠሩ ይደረጋል ፡-

የክልሉን የፒስካፕ ግዥ የሚያከናውን ሲሆን ከተጠቃሚ ተቋማትና ፕሮግራሞች ጋር በቅንጅት ይሠራል ፡-

የሚያስፈልጉ TOR ያዘጋጃል ፡፡

የዕቃዎች ዝርዝር / Technical specification / ያዘጋጃል በተዘጋጁት ላይም ግምገማ ያደርጋል ፡-

የኮንትራት ውል ያዘጋጃል ፡፡

ኮንትራቶችን በቢሮው አመራር ያስተዳድራል ይመራል ፡፡

## 4.5 የጋር የሆነ የመንግሥትና የአባዳሪ ድርጅቶች የግምገማ ሥርዓት / በ " PIP " ገጽ 18 / በመንግሥትና በአባዳሪዎች ጥምረት የተቋቋመ ኮሚቴ ነው ፡፡ አባሉቱም በመንግሥት በኩል

የአቅም ግንባታ ሚኒስቴርና

የፋይናንስ ኢ/ል/ሚኒስቴር ዋነኞቹ ናቸው ፡፡ ሌሎች ተሳታፊና አስፈጻሚ መ/ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ ተሳታፊ ናቸው ፡፡

ከአበዳሪ ድርጅቶች በኩል ፡-

የአፍሪካ ልማት ባንክ / AFDB/

የካናዳ ልማት ድርጅት / CIDA /

የአየርላንድ የልማት ኮርፖሬሽን / DCI /

የእንግሊዝ የልማት ድርጅት / DFID/

የአውሮፓ ኮሚሽን / EC /

የፊንላንድ ልማት ድርጅትና መንግሥት

ፈረንሳይ ልማት ድርጅትና መንግሥት

ጀርመን ተራድኦ ድርጅትና መንግሥት

ኢጣሊያን ተራድኦ ድርጅትና መንግሥት

ጃፓን ተራድኦ ድርጅትና መንግሥት

ኒዘርላንድ ተራድኦ ድርጅትና መንግሥት

የስዊዲን ልማት ድርጅት / SIDA /

13. የተባበሩት መንግሥታት ልማት ድርጅት / UNDP /

14. የአሜሪካን ልማት ድርጅት / US AID/ እና

የዓለም የልማት ድርጅት / IDA / ናቸው ፡፡

ይህ ኮሚቴ በመንግሥትና በ IDA ሊቀመንበርነት በጋራ የሚመራ ነው ፡፡ በአንድ ማዕቀፍ / pooling / በተቀመጠ ገንዘብ አጠቃቀም ላይ በጋራ የሚነጋገር ሲሆን አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ደግሞ በአንድ ማዕቀፍ ባልተቀመጡ / non - pooling / የቴክኒክ ድጋፍ ዕርዳታዎች ላይ ይወስናል፡፡

የአበዳሪዎች ሊቀመንበርነት ተራ በተራ የሚቀያየር ይሆናል ፡፡

በጋራ መረጃ ይለዋወጣል ፥ በጋራ ዕቅዶችን ያዘጋጃል ፥ ይገመግማል ፥ ይከታተላል ፡፡

ተሳታፊ አበዳሪዎች የዓመት ዕቅድን ፥ ዓመታዊ የዕቅድ አፈጻጸምና የግዥ ግምገማ (ቅድመ ግዥና ድህረ ግዥ / Prior and post review / ያደርጋሉ፡፡

ከዓመታዊ ስብሰባ ሌላ በተከታታይ በየሩብ ዓመቱ በጋራ ይሰበሰባሉ አፈጻጸሙን ይገመግማሉ መመሪያ ይሰጣሉ ፡፡